# የእከክ በሽታን መከላከያ መንገዶች

**በሽታው ከያዘው ሰው ጋር ንክኪ አለማድረግ**
ንክኪ ማድረጉ የግድ ከሆነ ንክኪ ከማድረግ በፊትና በኋላ በቂ ውሃ ካለ እጅን በውሃና በሳሙና መታጠብ፣ እንዲሁም በማከክ ቁስሉ እዳይባባስ ጥፍሮችን አሳጥሮ መቁረጥ

**በቂ ውሃ ካለ የግል ንፅህናን በሚገባ መጠበቅ**
ሰውነትንና ፀጉርን መታጠብ እንዲሁም ልብስን በየጊዜው ማጠብ

እከክ ከያዘው ሰው ጋር የሰውነት ንክኪ ያደረጉ ሰዎች ምልክቱ ባይታይባቸውም መታከም አለባቸው፣

በእከክ ዳግም መያዝን ለመከላከል ሁሉም ንክኪ ያላቸው ሰዎች በተመሳሳይ ጊዜ መታከም አለባቸው፣

ህክምና በተደረገ ከ 2-4 ሳምንት በኋላ የማሳከክ ችግር ከቀጠለ ቶሎ በአቅራቢያዎ ወደሚገኘው የህክምና ተቋም በመሄድ የጤናባለሙያ ማማከርያስፈልጋል።

## ለበለጠ መረጃ
## በ 952 የስልክ መስመር
## ይደውሉ



## የእከክ በሽታን እንከላከል፤
## በሽታው ከያዘንም ቶሎ
## ህክምና አግኝተን እንዳን

## የእከክ በሽታ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

እጅግ የተለመዱት የእከክ በሽታ ምልክቶች በጣም ማሳከክ እና ነጠብጣብ መሰል የቆዳ ላይ ሽፍታዎች ናቸው።

ሽፍታው በማንኛውም የቆዳ ክፍል ሊከሰት ቢችልም በተለይ ግን በእጅ፣ በጣቶች መካከል፡ በጥፍሮች ዙሪያ፡ የሰዓት ማሰሪያ አካባቢ፣ የክርን መታጠፊያ፣ በጡት፣በብብት፣ በወገብ ዙሪያ እና በብልት አካባቢ ሽፍታው የሚከሰትባቸው ዋነኞቹ የሰውነት ክፍሎች ናቸው።

የማሳከክ ስሜት በሁሉም ሰው ላይ ላይከሰት ይችላል።





## የእከክ በሽታ ተገቢውን ሕክምና ካላገኘ አይድንም

ያለትክክለኛው ህክምና የእከክ በሽታ የተወሳሰበ ችግር ሊፈጥር ይችላል።

በባለሙያ የታዘዘውን መድኃኒት በትዕዛዙ መሠረት ሳያቋርጡ መጠቀም ያስፈልጋል። መድሃኒቱ የሚዋጥ ወይም የሚቀባ ሊሆን ይችላል።

## መድሃኒት በሚወሰድበት ወቅት

አንሶላዎች፣ ብርድልብሶች፣ ጋቢ፣ ነጠላ እና ሌሎች የተለበሱ ልብሶችን በፈላ ውሃ አጥቦ ለ3ቀናት ፀሐይ ላይ ማስጣት በፀሐይ ላይ ማስጣት

በቂ ውሃ በሌለበት ሁኔታ ልብሶቹን በሙሉ እንደገና ከመለበሳቸው በፊት እስከ 3 ቀን ድረስ ፀሐይ ላይ ማቆየት ወይም በፌስታል አስሮ ለ3 ቀን ማስቀመጥ